ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረጀብ 10/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስቴር 11/2022 ግ.

# መፋታት የሚያስከትለው አደጋ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**"والصُّلْحُ خَيْرٌ"**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የዐረፍተ ነገሩ ትርጉም፡ (መታረቅም መልካም ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

የእስልምና እምነት ለትዳር ሕይወት ልዩ ቅድስናና የላቀ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ እንድሁም ማረፊያነትን፣ መተዛዘንንና የጋራ መከባበረን መሰረት በማድረግ ለዚህ የትዳር ሕይወት መረጋጋት፣ ትስስር፣ ጥንካሬና ዘላቂነት ዋስትና ይሆን ዘንድ ቋሚ ደንብ አስቀምጧል አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"وَعَاشِرُوهُنَّ بِالمَعْرُوفِ"

(በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በጣም ደጋችሁ ለቤተሰቡ በጣም ደግ የሆነ ሰው ነው)፡፡

ቅዱስ ቁርአንን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው አላህ (ዐ.ወ.) እሱን ማክበሩ ግድ መሆኑን ለማመልከትና እሱን ማፍረስና ማናጋት የሚያደርሰው አደጋ ከፍተኛ መሆኑን ለማስጠንቀቅ ትዳርን የጠበቀ ኪዳን እያለ የሚጠራው መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ አላህ(ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"وَأَخَذْنَ مِنْكُمْ مِيثَاقًا غَلِيظًا".

( ከእናንተ ላይም (ሴቶች) የጠበቀ ኪዳንን የያዙባችሁ ሲኾኑ)፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ህግጋት ባልና ሚስት እያንዳዳቸው የሕይወት አጋራቸውን ግልጽ በሆነ እይታ እንዲመለከቱ፣ በትዳር ሕይወት ያለውን መልካም ጎን በጥሞና እንዲያጤኑ፣ እሱን ዘላቂ ማድረግ ያቀፋቸውን እንደማረፊያነት፣ መንፈሳዊ እርካታና የዝርያ ደስታ ያሉ ጠቀሜታዎችን እንዲያስብ ይገፋፋሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"وَعَاشِرُوهُنَّ بِالْمَعْرُوفِ فَإِنْ كَرِهْتُمُوهُنَّ فَعَسَى أَنْ تَكْرَهُوا شَيْئًا وَيَجْعَلَ اللَّهُ فِيهِ خَيْرًا كَثِيرًا"

(በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፡፡ ብትጠሉዋቸውም (ታገሱ)፡፡ አንዳችን ነገር ብትጠሉ አላህም በእርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይቻላልና፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ ( አንድ ምእምን አንድትን ምእምን አይጥላ፡፡ ምክንያቱም ከሷአንድን ጠባይ ቢጠላም ከሷ ሌላ ጠባይን ሊውድ ይቻላልና)፡፡ ምሉእነት ለአላህ ብቻ ነው፡፡ ጥብቅነትም ለነብያቱና ለመልእክተኞቹ ብቻ ነው፡፡

የሚከተለው ግጥም ደራሲ አጅጉን የሚደነቅ ነው፡

ማንነው እሱ ሁሉም ጠባዩ ሊወደድለት የሚችል

እንድ ሰው ጨዋ ነው ለመባል ነውሮቹ በቁጥር የሚወሰኑ መሆናቸው በቂው ነው፡፡

የትዳር ሕይወት የቤትስብ ደስታ ጥራትን የሚያደፈርሱ አንዳንድ የአመለካከት ልዩነቶች ሊኖሩበት የሚችል መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በመሆኑም ቅዱስ ቁርአን ለዚህ ዓይነቱ በሽታ ፍቱን የተባሉ የፈውስ መድሃኒቶችን ያስቀመጠና ደግ ነገር ሁሉ በእርቅ፣ በመስማማት፣ አንዱ ሌላውን በማስደሰትና ውለታን በመዋል የታቀፈ መሆኑን ሲያብራራ እናገኘዋለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"وَإِنِ امْرَأَةٌ خَافَتْ مِنْ بَعْلِهَا نُشُوزًا أَوْ إِعْرَاضًا فَلاجُنَاحَ عَلَيْهِمَا أَنْ يُصْلِحَا بَيْنَهُمَا صُلْحًا وَالصُّلْحُ خَيْرٌ وَأُحْضِرَتِ الْأَنْفُسُ الشُّحَّ وَإِنْ تُحْسِنُوا وَتَتَّقُوا فَإِنَّ اللَّهَ كَانَ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرًا"

(ሴትም ከባልዋ ጥላቻን ወይም ፊቱን ማዞርን ብታውቅ በመካከላቸው መስማማትን ቢስማሙ በሁለቱ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ መታረቅም መልካም ነው፡፡ ነፍሶችም ንፍገት ተጣለባቸው፡፡ መልካምም ብትሠሩ ብትጠነቀቁም አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው፡፡)

ነግሩ ከባልና ሚስት ቤተሰቦች አስተዋይ፣ ጥበበኛ፣ በዘርፉ ልምድ ያላቸው፣ ጻድቃንና ፈሪሃ አላህ የሆኑ ወገኖች ጣልቃ መግባትን የሚያስፈልግ በሚሆንበት ጊዜ ማስታረቅና አለመግባባትን ለማስወገድ በማሰብ የተከበረ ሽምግልና መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"وَإِنْ خِفْتُمْ شِقَاقَ بَيْنِهِمَا فَابْعَثُوا حَكَمًا مِنْ أَهْلِهِ وَحَكَمًا مِنْ أَهْلِهَا إِنْ يُرِيدَا إِصْلَاحًا يُوَفِّقِ اللَّهُ بَيْنَهُمَا إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيمًا خَبِيرًا"

(የመካከላቸውንም ጭቅጭቅ ብታውቁ ከቤተሰቦቹ ሽማግሌን ከቤተሰቦችዋም ሽማግሌን ላኩ፡፡ ማስታረቅን ቢሹ አላህ በመካከላቸው ያስማማል፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነውና፡፡)

በዚህም አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ ታላቅ ምንዳ ይገኛል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"لا خَيْرَ فِي كَثِيرٍ مِنْ نَجْوَاهُمْ إِلَّا مَنْ أَمَرَ بِصَدَقَةٍ أَوْ مَعْرُوفٍ أَوْ إِصْلَاحٍ بَيْنَ النَّاسِ وَمَنْ يَفْعَلْ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ مَرْضَاتِ اللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا"، ويقول نبينا (صلى الله عليه وسلم): (أَلَا أُخْبِرُكُمْ بِأَفْضَلَ مِنْ دَرَجَةِ الصَّلَاةِ وَالصِّيَامِ وَالصَّدَقَةِ؟ قَالُوا: بَلَى، قَالَ: إِصْلَاحُ ذَاتِ الْبَيْنِ).

(ከውይይታቸው በምጽዋት ወይም በበጎ ሥራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በብዙው ውስጥ ደግ ነገር የለበትም፡፡ ይኸንንም (የተባለውን) የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን፡፡)

ጉዳዩ የትዳር ሕይወትን ለማስቀጠል በፍጹም የማይቻልበት ደረጃ በመድረሱ የሚጠራጠሩ ቢሆንም እንኳ የእስልምና ህግጋት የችግሩ አውሎ ንፋስ እስከሚያልፍ፣ ልብ እስከሚረጋጋና መንፈስ እስከምትጸዳ ድረስ መታገስ አእምሮን በማሰራት ማስተዋል አስፈላጊ መሆኑን የሚመክሩ ሲሆን በዚህም ለቤተሰብ ህልውና መቀጠል አጽንኦት በመስጠት እንደገና ማሰብ ሊከሰትና መስማማትም ሊመጣ እንደሚችልም ያበስራሉ፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትናሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

ፍች የእስልማና ሃይማኖት መመሪያ በማረፊያነት፣ በመፋቀርና በመተዛዘን እንድመሰረት ያዘዘውን ቤት ማፍረስ መሆኑ እንድሁም በቤተሰብ ብሎም በመላ ማህበረሰቡ አሉታዊ ተጽእኖና የተለያዩ ችግሮችን የሚያስከትል መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ የወላጆች መለያየት በተለይም በልጆች ላይ የመንፈስ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮች ያስከትላል፡፡ በዚህ የቤተሰብ መበታተን ምክንያት የመልካም አስተዳደግና

የትክክለኛ እድገት መሰረት መዋቅሮችን ያጣሉ፡፡ ይህም ለመንፈሳዊ ውዝግብና ለትምህርት መዘግየት ይዳርጋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በቀላሉ የጠባይ ማፈንገጥ ችግር ላይ ይውደቃሉ ወይም በጸንፈኛ፣ ህውከት ፈጣሪና ሽብር ቡድኖች ወጥመድ ይገባል፡፡ በመሆኑም ሰይጣን የቤተብ መዋቀር አእማድን ለመጣል ከባልና ሚስት መካከል የማሳሳት ቤት ስራውን ያለማቋረጥ ያከናውናል፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ዳቢሎስኮ ዙፋኑን ውሃ ላይ ያቆማል፡፡ ከዚያም የጦር ቡድኖችን በያቅጣጫው ያሰማራል፡፡ ለሱ በደረጃ በጣም  ቅርብ የሚሆነው በሰው ልጅ ለይ ከፍተኛ ፈተና የሚያደርሰው ተላላኪ ነው፡፡ ከነሱ አንድ ከሱ ጋ ይቅርብና «እኔ እንድህ አደርጊያለሁ፡፡ አንድህም አድርጊያለሁ ይላል፡፡ እሱም አንተ ምንም አልፈጸምክ ይለዋል፡፡ ከዚያም ሌላኛው ይቀርብና እኔ ደግሞ እሱና ሚስቱን ሳላለያይ አልተውኩትም ይላል፡፡ ይህን ወደሱ ያስጠጋውና አዎ አንተ ጥሩ ሰርተሃል ይለዋል»)

ይህን ማለትም እኛ ከሰይጣን የወጥመድ ገመዶች ለማምለጥ ጠንከረን መስራት እንድሁም ብልህና ንቁ መሆን ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

ከሁሉም የቤተሰብ አባል መካከል መስማማት፣ መከባበርና መዋደድ ሲሰፍን እንዴት ደስ ይላል፡፡ በሱም ከመላ ማህበረሰቡ መካከል መተሳሰርና መረጋጋት እውን ይሆናል፡፡

ጌታችን ሆይ! በልቦቻችን መካከል አስማማልን፡፡ በመካከላችንም ያለውን ሁኔታ አሳምርልን፡፡ አሚን